ይህ ፅሁፍ ኤፍ ኤስ ኤስ ACRC ከተሰኘ የጥናትና ምርምር መረብ ጋር በመተባበር በቅርቡ ከተገበረው በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ጉዳዮች ዙርያ የተኮረ የጥናትና የጥናት ውጤት ቅበላ (Research Uptake) ፕሮጀክት የመነጩና ለአንባብያን በሚመች መልኩ ተዘጋጅተው በሪፖርተር ጋዜጣ በ "***ምርምር ለልማት***" አምድ ታትመው የወጡ ፅሁፎች ናቸው።

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (ኤፍ.ኤስ.ኤስ.) በማሕበራዊና ልማታዊ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ጠለቅ ያለ ጥናትና ምርምር የሚያካሂድና፤ ባለድርሻ አካላት በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውይይት እንዲያደርጉ መድረኮችን የሚያዘጋጅ፤ መንግስታዊ ያልሆነና

ለትርፍ ያልተቋቋመ ሀገር-በቀል የሲቪክ ማሕበረሰብ ድርጅት ነው። ባለፉት 25 ዓመታት ድርጅቱ ከበርካታ ለጋሽ ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ እና በትብብር በበርካታ የፖሊሲ ጉዳዮች ዙርያ ፖሊሲ ተኮር ምርምርና የህዝባዊ ውይይት መድረክ ፕሮጀክቶችን

ያካሄደ ሲሆን ውጤቶቻቸውንም በተለያዩ ህትመቶችና በሪፖርተር ጋዜጣ ምርምር ለልማት የተሰኘው ይህው አምድን ጨምሮበሳምንታዊ የራድዮ ፕሮግራሞች፣ በቴሌቪዥን እንዲሁም ኦፊሴላዊ ድረ-ገፁ www.fss-ethiopia.org ና ማህበራዊ ትስስር ገፆቹ አማካኝነት ለተለያዩ የባለድርሻ አካላትና ለህዝብ ተደራሽ ያደርጋል።

በዚህ አምድ፣ የአፍሪካ ከተሞች የምርምር ጥምረት ‹‹African Cities Research Consortium (ACRC) ከተባለ ድርጅት ጋር በመተባበር በተተገበረው በውጣቶች አቅምና ችሎታ፣ በቤቶች ልማትና መዋቅራዊ ለውጥ በሚሉ ሰፋፊ ርዕሶች ላይ በተካሄዱ ጥናቶች ውጤቶችን የሚጋራት (Research Uptake) ፕሮጀክት ላይ የተመሰረቱ የምርምር ውጤቶች ለአንባቢያን በሚመች መልኩ ተዘጋጅተው ለአራት ተከታታይ ሳምንታት የሚቀርቡ ሲሆን በዚህ በመጀመርያው ክፍል በወጣቶች ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ፅሁፍ ቀርቧል።

## ኢትዮጵያ በ2050 ፡ የሥነ ሕዝብ ጸጋ ለኢኮኖሚ ዕድገት ለመጠቀም ትኩረት የሚያሻው የወጣቶች የሥነ ተዋልዶ ጤና ጉዳይ

**በኤፍሬም ብርሀኑ**

ዴክላን ዋልሽ፤ የኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ አምደኛ፤ እ.አ.አ. ኦክቶበር 28 2023 ዓ.ም. "ዓለማችን የበለጠ አፍሪካዊ እየሆነች ነው" በሚል ርዕስ ባሰፈሩት ጽሑፍ፤ የአፍሪካ የሕዝብ ብዛት አሁን ካለበት 1.4 ቢሊዮን እ.አ.አ. በ 2050 ዓ.ም. ከሩብ ምዕተ ዓመት በኃላ፤ 2.5 ቢሊዮን እንደሚሆን፤ ይህም ከዓለማችን የሕዝብ ቁጥር ምጣኔ 25% የሚሆነውን እንደሚይዝ፤ በዚህም ከ 4 የዓለማችን ሰዎች ውስጥ አንዱ አፍሪካዊ እንደሚሆን፤ በወጣትነት የእድሜ ክልል 15-24 ከሚገኙት ደግሞ ከሦስቱ አንዱ አፍሪካዊ እንደሚሆን የተባበሩት መንግስታት ጥናት ዋቢ አድርጎ ይገልጻል። ለማነፃፀር ያህል እ.አ.አ. በ1950 ዓ.ም. የአፍሪካውያን ህዝብ ብዛት ከዓለም 6% ብቻ ነበር።

የአፍሪካዉያን አማካኝ እድሜ 19 መሆኑን፤ ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት ያላት ህንድ ይኸ ምጣኔ 28 ሲሆን፤ የቻይናና አሜሪካ በተመሳሳይ 38 መሆኑን፤ ይኸም ለአፍሪካ መጪው ግዜ ብሩህ መሆኑ ማሳያ መሆኑን ይጠቅሳሉ። የአፍሪካ "የወጣቶች ማዕበል" የዓለም የፖለቲካ፤ ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚ የስበት ማዕከል እንዲሆን ያስገድደዋል። በተለይ በኢኮኖሚ የበለጸጉ የዓለማችን አገራት፤ የወሊድ ምጣኔ እጅጉን እየቀነሰ መሄድ ከዚህም ጋር በተያያዘ አማካኝ እድሜ እየጨመረ፤ አብዛኛው ህዝባቸው በሽምግልና እድሜ ክልል የሚገኝ መሆኑ፤ የአፍሪካ አህጉር የቴክኖሎጂ፤ የፈጠራ፤ የሳይንስና ምርምር ልህቀት፤ የፋሽን፤ የሙዚቃ፤ የኢንደስትሪ መናኸሪያ እንደምትሆን፤ "ጨለማው አህጉር" በሚልና በሌሎች የተዛቡ ትርክቶች የምትገለጽ እንደማትሆን ግምቱን ያጋራል። በፍጥነት እያደገ ያለው የአፍሪካ የፊልምና የሙዚቃ ኢንደስትሪ እ.አ.አ. 2030 20 ቢሊየን ዶላር ይደርሳል ተብሎ እንደሚገመት ይኸም 20 ሚሊዮን ለሚሆኑ ዜጎች የስራ እድል እንደሚፈጥር የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፤ ሳይንስና የባሕል ተቋም ግምት ያሳያል።

በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠሩ በምርታማ የእድሜ ክልል የሚገኙ ሸማቾችን ፍላጎት ለማርካት የዓለማችንን ትላልቅ ኩባንያዎች አፍሪካን መዳረሻ እያደረጓት መሆኑ፤ ለዚህ እንደማሳያ ይጠቅሳል። ሒልተን ሆቴል በቀጣይ አምስት አመታት 65 አዳዲስ ሆቴሎች በአፍሪካ ለመክፈት ማቀዱን አሰታውቋል። አፍሪካውያን ሚሊየነሮች ቁጥር በፍጥነት እያደገ መሆኑ፤ እ.አ.አ. በ 2027 768,000 እንደሚደርስ የክሬዲት ስዊዝ ጥናት ዋቢ አድርጎ ይገልጻል።

የቻይናና ህንድ በ21 ክ/ዘመን መባቻ ያስመዘገቡት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት አንዱ የዓለማችን አበይት ለውጥ ሲሆን የአፍሪካ "የወጣቶች ማዕበል" ደግሞ ሌላው የዓለማችን ትኩረት የሚስብ ቀጣይ አጀንዳ መሆኑ የግድ መሆኑን የቀድሞው የተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ዋና ጸሐፊ ካርሎስ ሎፔዝ ይገልጻሉ።

በበርካታ የዓለማችን አገራት፡ የወሊድ ምጣኔ ማነስ፤ የህዝብ ቁጥር እንዲቀንስና፤ በጎልማሳነት የእድሜ ክልል የሚገኙ ሰዎች ቁጥር እንዲጨምር ምክንያት መሆኑ ይታወቃል።

ከድህነት ወለል በታች ያሉ አፍሪካውያን ቁጥር አሁንም ትልቅ መሆኑ፤ በየዓመቱ የስራ ገበያውን የሚቀላቀሉ ወጣቶች ውስጥ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ብቻ የስራ እድል እንደሚያገኙ፤ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትሉት ተጽዕኖ ተዳምሮ ለአፍሪካ እድገት ማነቆ ሆነው እንደሚቀጥል ይታመናል።

**ኢትዮጵያ በ2050**

የኢትዮጵያ የህዝብ ብዛት እ.አ.አ. በ2020 ከነበረበት 115 ሚሊዮን፤ በ 2030 145 ሚሊዮን እንዲሁም በ2050 205 ሚሊዮን እንደሚደርስ ይገመታል። እንደ የተባበሩት መንግስታት የምግብና የእርሻ ድርጅት ግምት ኢትዮጵያ የነፍስ ወከፍ ገቢ እ.አ.አ. 2015 ዓ.ም. ከነበረበት 700 ዶላር በ 2050 5,500 ዶላር እንደሚደርስ ይጠቁማል። በከተሞች የሚኖረው የህዝብ ብዛት ከአጠቃላዩ 40% እንደሚሆን ይገመታል።

**ኢትዮጵያ ከዚህ ለመጠቀም፤ ምን ላይ ቅድሚያ ትስጥ?**

የወጣቶች የሥነ ተዋልዶ ጤና ማሻሻል፤ ኢትዮጵያ የሰው ኃይሏን በማጎልበት ኢኮኖሚዋን ለማሻሻል ወሳኝ ሚና ይጫወታል። የጤና ሚኒስቴር ከ 2013-2018 ዓ.ም. እየተገበረው የሚገኘው የወጣቶች የጤና ስትራቴጂ፤ እድሚያቸው 15-19 ባሉ ወጣት ሴቶች ከወሊድ ጋር የተያያዘ የሞት ምጣኔ አሁን ካለበት 0.39 ወደ 0.29 ለመቀነስ፤ በዚሁ እድሜ የሚከሰተውን እርግዝና ከ 12.5 ወደ 7 መቀነስ፤ 15-24 እድሜ ባሉ ወጣቶች የኤች.አይ.ቪ.. ኤድስ ስርጭትን 0.2% ወደ 0.1% እንዲሁም፤ ወጣቶች ወሲብ የሚጀምሩበትን እድሜ አሁን ካለበት 16.4 ወደ 17 ለማሳድግ እቅድ ተይዛል። የማስፈጸሚያ ስልት ተደርገው ከተለዩት መካከል፤ የወጣቶችን ግንዛቤ ማሳደግ፤ የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን ማስፋት፤ የጤና አገልግሎት ጥራት ማሻሻል ላይ ትኩረት አድርጓል።

**አሁናዊ ሁኔታው ምን ይመስላል?**

የማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ እ.አ.አ. በ2016 ዓ.ም. ባወጣው የሥነ ህዝብ ጥናት ውጤት መሰረት፤ እድሜያቸው 10-29 የሚሆኑት 38.5 ሚሊዮን እንደሆነ ይኸም ከአጠቃላይ የህዝብ ብዛት 42% እንደሆነ፤ ከ 10-24 ያሉት ደግሞ 33% እንደሚሸፍኑ ይገልጻል። አብዛኞቹ በታዳጊና ወጣትነት የእድሜ ክልል የሚገኙ የኃብረተሰብ ክፍሎች የሚኖሩት በገጠር ነው። በተለይ በታዳጊ የእድሜ ክልል ያሉ 10-14 ከሆኑት 81-82%፤ ወጣቶች 25-29 ደግሞ 74-75% የሚሆኑት በገጠር እንደሚኖሩ ያሳያል።

የጤና አገልግሎት ተደራሽነት በተመለከተ፤ 44.7% የሚሆኑ የጤና ተቋማት ብቻ ለታዳጊዎችና ወጣቶች ተስማሚ የሆነ አገልግሎት እንደሚሰጡ፤ ከነዚህ ውስጥ ደግሞ፤ 11% ብቻ አንድና ከዛ በላይ ለታዳጊዎችና ወጣቶች ተስማሚ የሆነ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሰለጠነ የሰው ኃይል እንዳላቸው፤ ከክልል ክልል የተለያየ ሁኔታ መኖሩንም ያሳያል። እንደማሳያ፤ ትግራይ 20%፤ አማራ 17% እና በደቡብ ክልል 16% መሆኑን ይጠቁማል። እንደ ጋምቤላ አይነት በማደግ ላይ በሚገኙ ክልሎች የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖሩን ይጠቁማል። ታዳጊዎችና ወጣቶች ውስን የሆነ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት ያላቸው መሆኑ፤ ይኸም የጤና መስጫ በአካባቢያቸው ያለመኖር፤ አገልግሎት ለማግኘት ረጅም ወረፋ መጠበቅ ግድ የሚል መሆኑ፤ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ርቀት፤ እንዲሁም ለአገልግሎት የሚከፈለው ክፍያ፤ ወጣቶች አገልግሎት እንዳያገኙ ተጽዕኖ መፍጠሩን ይገልጻል።

የተለያዩ የሥነ ተዋልዶ የጤና አገልግሎቶች በታዳጊዎችና ወጣቶች ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት በምንመለከትበት ግዜ፤ በተለይ በገጠር የሚኖሩና፤ የትምህርት ደረጃቸው ዝቅተኛ የሆነ ወጣቶች ስለ ሥነ ተዋልዶ ጤና በጥቅል እንዲሁም ስለ ቤተሰብ ዕቅድ አጠቃቀም ብዙ መስተካከል የሚገባቸው የተዛቡ አመለካከቶች መኖራቸው ይስተዋላል። ትዳር ከመሰረቱ ሦስት ወጣቶች ሁለቱ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት እንደማይጠቀሙ፤ ይኸም በቂ ግንዛቤ ካለመኖር ጋር የተያያዘ መሆኑን እንዲሁም ደግሞ ኃይማኖትም እንደምክንያት ይጠቀሳሉ።

ከላይ በተዘረዘሩትና ሌሎች ምክንያቶች ሳቢያ ታዳጊዎችና ወጣቶች ስለ ሥነ ተዋልዶ ጤና ያላቸው ግንዛቤ አናሳ መሆኑን፤ በቤተሰብና ማኅበረሰብ ደረጃ፤ ሰለ ወሲብ በግልጽ የመነጋገር ባህል ባለመዳበሩ ምክንያት፤ ወላጆችም ከልጆቻቸው ጋር ሥነ ተዋልዶ ጤና አስመልክቶ ለመወያየት የሚያስችል በቂ ግንዛቤ ባለመኖሩ፤ የትምህርት ስርዓቱ ታዳጊዎችና ወጣቶች በቂ ግንዛቤ ለማስጨበት የማይችል መሆኑ፤ ታዳጊዎችና ወጣቶች ለተለያዩ ችግሮች ሲጋለጡ ይታያል።

**አስፈላጊ የፖሊሲ ምክረ ኃሳቦች**

ለታዳጊዎችና ወጣቶች ሥነ ተዋልዶ ጤና መሻሻል ብሎም ለወደፊት ምርታማና የሆነ ዜጋ ለማፍራት በሚደረገው ሀገራዊ ጥረት ውስጥ በጤና ሚኒስቴር ከሚደረገው ጥረት በተጨማሪ የሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላት ርብርብ ይፈልጋል። ከዚህ በመቀጠል፤ እነዚህን የፖሊሲ ምክረ ሃሳቦች ለመጠቆም እሞክራለሁ።

**ቅንጅታዊ አሰራር**

ለታዳጊዎችና ወጣቶች የጤናም ሆነ መሰል ማኅበራዊ አገልግሎቶች የተለያዩ ባላድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሰራር መኖር የግድ ይላል። አንዱና ዋነኛው ታዳጊዎችና ወጣቶች የት ይገኛሉ ወይም ደግሞ አገልግሎቶቹን በምን ዓይነት መንገድ ተደራሽ ማድረግ ይቻላል የሚለው አበይት ትኩረት ከሚሹ ጉዳዮች አንዱ ነው።

ታዳጊዎችንና ወጣቶችን ልናገኝ ከምንችልባቸው ቦታዎች በዋናነት የሚጠቀሱት መካከል፤ የወጣት ሰብዕና ልማት ማዕከላት እንዲሁም ት/ቤቶች የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳሉ። የወጣት ሰብዕና ልማት ማዕከላት ፤ ለወጣቶች አካላዊ፣ አእምሯዊና ስነ ልቦናዊ እድገት ኢጋዥ የሆኑ ወጣት ተኮር ማህበራዊ አገልግሎቶች የሚሰጡበት ተቋም ነው።

እ.ኤ.አ. ከ1997 ዓ.ም. ወዲህ በመላው አገሪቱ 3000 ባላይ የሚሆኑ የወጣቶች የሰብዕና መገንቢያ ማዕከላት በመንግስት ወጪ ተገንብተዋል። እነዚህ ማዕከላት፣ የወጣቶችን አዳዲስ ሀሳቦችን የመፍጠርና የመቀበል እምቅ አቅምና ብሩህ አእምሮ ለማጎልበት፤ ወጣቶች በሀገሪቱ በተጀመሩት የልማት እንቅስቃሴዎች ንቁ ተሳተፎ እንዲኖራቸውና በተሳትፏቸው ልክ ተጠቃሚ እንዲሆኑ፣ ካላስፈላጊ ማህበራዊ ጠንቆችና አሉታዊ መጤ ባህሎች ርቀው የሃገራቸውን ባህሎችና እሴቶችን እንዲያውቁና እንዲያከብሩ፣ ያላቸውን ተሰጥኦና ክህሎት እንዲያዳብሩ እና ከአቻዎቻቸው ጋር በመምከር ልምድና ተሞክሮ እንዲለዋወጡ እንዲረዷቸው ባማሰብ የወጣቶች ስብዕና ልማት ማእከላት በሃገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ተገንብተው አገልግሎት እንዲሰጡ በርካታ ተግባራት ሲከናወኑ ቆይተዋል፡፡

የወጣቶች የመዝናኛና የእረፍት ጊዜ ማሳለፊያ ችግሮችን ለመፍታት የየአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የስብዕና ልማት ማዕከላት በሁሉም ወረዳዎች ተደራሽ መሆን እንዳለባቸው የኢትዮጵያ ወጣቶች የእድገት ፓኬጅ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የፌዴራልና የክልል መንግስታት ከፍተኛ በጀት በመመደብ እና የግንባታ ቦታዎችን በማመቻቸት በርካታ ማዕከላት እንዲገነቡ በማድረጋቸው ቁጥራቸው የማይናቅ ወጣቶች በነዚህ ማዕከላት እየተጠቀሙ ይገኛሉ፡፡

የወጣት ሰብዕና ልማት ማዕከላት በአራት ይከፈላሉ። ይኸውም ሞዴል፤ ሁለገብ፤ መለስተኛ፤ አነስተኛ ተብለው ተለይተዋል። ሞዴል የሚባሉት ማዕከላት 16 የሚሆኑ የተለያዩ አገልግሎቶች ለወጣቶች ይሰጣሉ፤ እነዚህም የቤተመፅሃፍት፤ የካፍቴሪያ፤ ወጣት-ተኮር የጤና አገልግሎቶች፤ ሁለገብ አዳራሽ፤ የቤት ውስጥ ጨዋታዎች፤ የቤት ውጭ ጨዋታዎች፤ የመረጃ ማዕከል/ ICT center/፤ የገላ መታጠቢያ፤ የኪነ ጥበባት፤ የስልጠና፤ የስነ ልቦና ድጋፍና ምክር፤ ሁለገብ ጂምናዚየም አገልግሎት፤ የበጎ ፈቃድ፤ የሚኒ ሚዲያ፤የፈጠራና ሰርቶ ማሳያ፤ መለስተኛ ሱቅ አገልግሎቶች ናቸው፡፡ ሁለገብ ማዕከላት 12 አገልግሎቶችን፤ መለሰተኛ 9፤ አነሰተኛ ደገሞ 5 አገልግሎት ይሰጣሉ። ሁሉም ዓይነት ማዕከላት ወጣት ተኮር የጤና አገልግሎት እንዲሰጡ ይጠበቅባቸዋል።

ማዕከላቱን በፌደራል ደረጃ የሴቶችና ማኅበራዊ ሚኒስቴር፤ በክልል ደረጃ ደግሞ የወጣቶችና ስፖርት ቢሮዎች በበላይነት ያስተዳድሯቸዋል።ወጣት ተኮር የጤና አገልግሎቶችን ተደራሽ ለማድረግ፤ ከጤና ሚኒስቴርና፤ መሰል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በቅርበት መስራት ይጠይቃል። የጤና ሚኒስቴር፤ ማዕከላቶቹን በሰለጠነ የሰው ኃይል ማጠናከር፤ የህክምና ቁሳቁሶች እንዲሁም መድኃኒቶች አቅርቦት በማሟላት እንደ አንድ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋም ሊጠቀምባቸው ይገባል።በአገር አቀፍ ካሉ 3000 ማዕከላት 50% ብቻ የተሟላ አገልግሎት እንደሚሰጡ መረጃዎች ያሳያሉ። ቅንጅታዊ አሰራር መኖር፤ ለሁለቱም ሚኒስቴር መ/ቤቶች ጠቃሚ መሆኑን ለማየት ይቻላል።

**የትምህርት ሴክተር ምላሽ**

የትምህርት ሴክተር የትምህርት አገልግሎት ከማዳረስ፤ ጥራት ያለው ትምህርት ተደራሽ ለማድረግ ከሚሰራው ስራ ውጭ፤ የታዳጊዎችንና የወጣቶችን የጤና ሁኔታ ለማማሻል የሚረዳ ስራ መስራት ካለባቸው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ግንባር ቀደሙ ነው። 47% የሚሆነው የኃብረተሰብ ክፍል ከ15 በታች መሆን፤ የሁለተኛና ለከፍተኛ ትምህርት እድሜ የደረሱትን ስንጨምር በብዙ ሚሊየን የሚቆጠሩ ታዳጊዎችና ወጣቶች በትምህርት ገበታ ላይ መሆናቸውን እንረዳለን።

በተለይ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ እንዲሁም በዩኒቨርስቲ የሚማሩ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ተማሪዎች፤ የጤና ሁኔታ ማሻሻል ላይ፤ ከጤና ሚኒስቴር ጋር በጋራ መሰራት ይገባዋል። በየአስር ዓመቱ ከለሳ የሚደረግለት የትምህርት ፍኖተ ካርታ፤ ባሳላፍነው ዓመት ሲሻሻል፤

የታዳጊዎችና ወጣቶች ሥነ ተዋልዶ ጤና የተመለከት ማስተማሪያ እንዲካተትበት የተደረገው ጥረት ሳይሳካ ቀርቷል። በትምህርት ፍኖተ ካርታው ውስጥ አስገብቶ ለታዳጊዎችና ወጣቶች እድሜያቸውን ያማከለ መረጃና ትምህርት የሚያገኙበት እድል ሳይሳካ ቀርቷል።

ኤች አይ ቪ ኤድስ በሀገራችን በከፍተኛ ደረጃ ተስፋፍቶ በነበረበት ግዜ፤ በተለይ ዩኒቨርሲቲዎች ኮንዶም ለወጣቶች በመጸዳጃ ቤት ለማኖር ብዙ ክርክር እንደነበረ የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ ያስታውሳል። የመጀመሪያ ትውልድ ዩኒቨርሲቲ ከሆኑት መካከል፤ ጅማ፤ መቀሌ፤ ባህር ዳር የመሳሰሉት እስከ 40,000 የሚጠጋ ተማሪ ያስተምራሉ። ሆኖም እስከ ቅርብ ግዜ ድረስ በየዩንቨርሲቲዎቹ የሚገኙ ክሊኒኮች ከጤና ሚኒስቴር ጋር ትሥሥር እንደሌላቸው፤ በዚህም የሚመደቡት የጤና ባለሙያዎች በቂ ስልጠና እንደማያገኙ፤ የመድኅኒትና ሌሎች ለህክምና የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች እጥረት እንዳለባቸው ይነገራል። ጸሐፊው በቅርብ ግዜ የተሳተፈበት የአዲስ አበባ ወጣቶች የጤና አገልግሎት የተመለከተ ጥናት እንደሚያሳየው በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና በዩንቨርሲቲ የሚገኙ ወጣቶች ተገቢ የሆነ የጤና አገልግሎት በትምህርት ቤታችው እንደማያገኙ ይገልጻሉ።

የጤና ሚኒስቴር ያስቀመጣቸውን ትላልቅ ግቦች ለማሳካት የወጣቶች ጉዳይ የሚመለከተው ቢሮ እንዲሁም የትምህርት ሚኒስቴር ቀና ትብብር ያስፈልገዋል።

**በጀት ለቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት**

የጤና ሚኒስቴር የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ፤ በተለይ የአጭርም ሆነ የረጅም ግዜ የቤተሰብ ዕቅድ በስፋት ለማቅረብ፤ ከመንግስት የሚመደበው በጀት እንዲጨምር ለማድረግ ግብ አስቀምጧል። የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ማስፋፋት ከጤና ባሻገር ለኢኮኖሚ ዕድገት ዓይነተኛ ሚና የሚጫወት በመሆኑ፤ ከመንግስት የሚመደበው በጀት እንዲጨምር በማድረግ፤ አሁን ባብዛኛው ከዓለም ዓቀፍ በጎ አድራጊ የልማት ድርጅቶች ፋይናንስ የሚደረገውን በጊዜ ሂደት ለመተካት ይረዳል። ከውጪ የሚመጣ የልማት ፋይናንስ፤ በብዙ ተግዳሮቶች ውስጥ የሚያልፍ በመሆኑ ከምንም በላይ ደግሞ እንደ ሀገር ተጽዕኖ ልናደርግበት የማንችል መሆኑ በግዜ ሂደት ራሳችንን ለመቻል ጥረት ማድረግ ይገባል። ኮቪድ በዓለም ላይ ያመጣው የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ፤ እንዲሁም የራሻና የዩክሬን ጦርነት ምክንያት፤ የእንግሊዝ መንግስት ለልማት ዕርዳታ የሚያውለውን ገንዘብ፤ ከአጠቃላይ ገቢው (ጂዲፒ) 0.7% ወደ 0.5% እንዲቀንስ አስገድዶታል። ዋን ካምፔን የተባለ ተቋም በሰራው ጥናት መሰረት፤ የእንግሊዝ መንግስት የበጀት ቅነሳ በኢትዮጵያ ብቻ 498 ሺህ ሴቶች ብቻ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት እንዳያገኙ ማድረጉን ይገልጻል።

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጤናና ማኅበራዊ እንዲሁም የበጀት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ፤ ለዚህ ጎዳይ አጽንኦት በመስጠት መንግስት ከታክስና ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች ለቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት የሚሆን ገንዘብ እንዲመድብ መከታተልና ማገዝ ይጠበቅባቸዋል።

ኢትዮጵያ በቀጣይ አስርት ዓመታት ዛላቂ ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማስመዝገብ፤ ድህነት ለመቀነስ የሚደረጉ ጥረቶች ከወዲሁ የወጣቶች ሥነ ተዋልዶ ጤና ማሻሻል ላይ ያተኮረ የፖሊሲ አቅጣጫ መከተል ይኖርበታል።